

2030

# ስልታዊ ዕቅድ (STRATEGIC PLAN)

**መንከባከብ/Nurture • ማስተማር/Educate • ስሜትን ማነሳሳት/Inspire**

*በሜይ (May) 8 ቀን 2025 ላይ*

Alexandria City Public Schools

# ዋና እሴቶች

በምንሰራው-ነገር ሁሉ፣ የACPS መማሪያ ማህበረሰብ - እነዚህን ዋና እሴቶችን - ይዞ-ለመኖር እየገፋበት-ይገኛሉ። እኛ...

### ሁሉን-ተቀባይ የሆነ (Welcoming)

በACPS ውስጥ፣ ሁሉንም ባለድርሻ-አባላቶች (stakeholders) - ደህንነታቸው-የተጠበቀ እና በደስታ-እንደተቀበልናቸው (welcomed) ስሜት እንዲሰማቸው፣ ንቁ እርምጃዎችን እንወስዳለን። በእኛ በር-በኩል የሚመጡትን ሁሉ-ተቀብለን፤ ልዩነቶቻችንን እናከብራለን - ምክንያቱም ልዩነታችን ትልቁ ጥንካሬያችን ነው-ብለን ስለምናምን ነው።

### ፍትሃዊ-እኩልነት ላይ ትኩረት ያደረገ (Equity-focused)

ትምህርትን-ለማግኘት እንቅፋት የሚሆኑ ነገርችን - በንቃት ለማስወገድ እንሰራለን።

### ኃይል-መስጠት-የሚችል (Empowering)

እያንዳንዱን ተማሪ እና የሠራተኛ-አባል፤ ተመራጭ ወደሆነው አቅማቸው እንዲደርሱ፣ ስሜታቸውን-እናነሳሳለን።

### ፈጠራዊ-የሆነ (Innovative)

በመማሪያ-ክፍል ውስጥ እና በስርዓቱ ዙሪያ ባሉት-ነገሮች ውስጥ፣ ችግሮችን-ለማስወገድ - ተነሳሽነትን እንፈጥራለን።

### በውጤት-ላይ ያተኮረ (Results-Driven)

ለመማር፣ ለማደግ እና በከፍተኛ-ደረጃዎች ውጤታማ ለመሆን - ትልቅ-ተስፋ ያላቸውን ግቦችን - አስቀምጠናል።

## የእኛ ተልዕኮ/Our Mission

እኛ - እያንዳንዱ ተማሪ ስኬት እንዲያገኝ፤ እንንከባከባለን፣ እናስተምራል እና ስሜታቸውን እናነሳሳለን።

## የእኛ ራዕይ/Our Vision

እያንዳንዱ-ተማሪ፤ በኮሌጅ፣ በስራ-መስክ፣ እና በማህበረሰብ - ለመበልጸግ ዝግጁ-ይሆናል።

# ማውጫዎች


ከጠቅላይ ስራ አስኪያጅ - የቀረበ መልዕክት ........................ 4

ከትምህርት ቤት ቦርድ - የቀረበ መልዕክት .......................... 5

ስለ አሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ........................................ 6

ለእኛ ስልታዊ-ዕቅድ አወጣጥ ያለው የአሰራር-አቀራረብ................ 8

የስልታዊ ዕቅድ-አወጣጥ ሂደት ................................ 9

የእድገት-ሂደት ቁጥጥር-ማድረግ ................................ 11

የእኛ፣ ስልታዊ ዕቅድ (Strategic Plan)........................ 12

የእኛ ባህል ............................................. 13

የእኛ ግቦች/Goals.......................................... 15

እናመሰግናለን ............................................ 22

ከACPS ጋር ግንኙነት-አድርጉ................................. 23

ተጨማሪ-አባሪ/Appendix ................................. 24



**የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች**
**(Alexandria City Public Schools)**

1340 Braddock Place • Alexandria, VA 22314

**ስልክ:** 703-619-8000

**ድህረ-ገጽ:** acps.k12.va.us

**Follow us:**

acpsk12 acpsk12 acpstv

# ከጠቅላይ ስራ አስኪያጅ/Superintendent

## የተላከ-መልዕክት

## ውድ የACPS ሠራተኞች፣ ቤተሰብ እና የማህበረሰብ

ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት፣ ስራችንን የሚመራንን - ከፍተኛ-እርምጃን የሚወስድ እና ተማሪን ማዕከል-ያደረገውን ራዕይ ያለውን — አዲሱን የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)ን የ2025-30 ስልታዊ ዕቅድ (Strategic Plan)ን መጀመር፤ ሳስታውቅ ደስታ-ይሰማኛል። ይህ ዕቅድ፤ እንደ ከዚህ-በፊት የነበረው ስልታዊ ዕቅዳችን (strategic plan) ተመሳሳይ ሆኖ፤ እያንዳንዱ ተማሪ - በኮሌጅ፣ የስራ-መስክ እና በሕይወቱ ውስጥ ለመበልጸግ የሚያስችለውን - እንክብካቤ-ማግኘቱን፣ ትምህርት-መማሩን፣ እና ስሜቱ-የተነሳሳ መሆኑን ለማረጋገጥ - የአጠቃላይ ማህበረሰባችንን የጋራ ቁርጠኝነት የሚያንጸባርቅ ነው።

ይህ ስልታዊ ዕቅድ (strategic plan) ሰነድ-ከመሆን-ብቻ - በበለጠ-ሁኔታ የሚገኝ — እርምጃ-ለመውሰድ ጥሪ-የሚያደርግ ነው። በእኛ - ፍትሃዊ-እኩልነት ለሁሉም (Equity for All) 2025 ዕቅድ በሚለው መሠረት-ላይ የሚገነባ እና እያንዳንዱ ተማሪ - የቀደመ-መነሻው ምንም-ሆነ ምን - እጅግ-በጣም ጥሩ የሆነ ትምህርትን ማግኘት መቻሉ ለማረጋገጥ ያለንን ትጋት በድጋሚ-የሚያረጋግጥ ነው።የተማሪዎችን እና ሠራተኞችን ልዩ-ሆነው የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች እና ሁኔታዎች ምላሽ-በመስጠት፤ ተሰጥዖአቸውን እና ሊሰሩ-በሚችሉትን ነገሮች ላይ ለመንከባከብ - ያለንን ቁርጠኝነት ይዘረዝራል። ይህ ዕቅድ፤ ምን-የበለጠ ለእኛ-ግድ-እንደሚለን ባለን ትኩረት ላይ ያጠናክራል: ሁሉንም-ተቀባይ የሆነ፣ ኃይልና-ጉልበት ሰጪ የሆነ እና ፈጠራዊ-የሆነ የመማሪያ አካባቢን - ለሁሉም ተማሪዎች እና ሠራተኞች - ወደፊት-እንዲበለጽጉ በማቅረብ-መንከባከብ።

ድምቀት እና ስብጥር-ያለው የትምህርት ቤት ክፍል/division እንደመሆኑ፣ ACPS፣ በአሁኑ-ጊዜ ከ118 አገሮች የመጡ እና 127 የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ 16,300 ተማሪዎችን እያገለገለ-የሚገኝ ሲሆን፤ ለሁሉም ተማሪዎች ሁሉን-አቀፍ እና ድጋፍ-ሰጪ የትምህርት አካባቢን በማቅረብ-ለመንከባከብ እና የበለጸገ የባህል  ውስብስብነትና-ስብጥርን የሚያንጸባርቅ እና ለሕዝብ ትምህርት ጠንካራ ቁርጠኝነት የሚሰጥ፣ ስልታዊ ዕቅድ (strategic plan)ን የሚያበረታታ-ነው።

### ሁሉንም-ያካተተ የትብብር ጥረት

የACPS የ2020-2025 ስልታዊ ዕቅድ (Strategic Plan)፤ በተማሪዎቻችን፣ በቤተሰቦቻችን፣ በሠራተኞቻችን እና በማህበረሰብ አባላቶች ድምፆች - ቅርጹን-ሲይዝ የቆየ ነው። ይህንን ራዕይ ለመንደፍ - ደከመን-ሰለቸን ሳይሉ ለሰሩት፣ የስልታዊ ዕቅድ-አወጣጥ ኮሚቴ (Strategic Planning Committee (SPC) እና ከ65 በላይ በትጋት-የሰሩ ግለሰቦች — ትምህርት-ሰጪዎች፣ ተማሪዎች፣ የትምህርት ቤት ቦርድ አባላቶች፣ ቤተሰቦች እና የማህበረሰብ ተወካዮችን ጨምሮ፣ ከልብ-የመነጨ ምስጋናዬን ማቅረብ እፈልጋለሁ። ይህ ዕቅድ፤ እውነተኛ-የሆነውን የትምህርት ቤታችንን ማህበረሰቦችን ፍላጎቶች እና ምኞቶች የሚያንፀባርቅ መሆኑን ለማረጋገጥ፣ የእናንተ - ጥልቅ-ፍላጎት፣ የሃሳብ-አመለካከቶች እና ቁርጠኝነት፤ ዋጋው-ተተምኖ የማያልቅ አድርጎታል።

ሂደቱ-በሚካሄድበት ወቅት ሙሉ፣ አዳምጠናል፣ በ'SPC' በተሰበሰበው አስተያየት ላይ መሠረት-አድርጎ፣ አቀራረባችንን በድጋሚ-አጣርተና እና ተምረናል። እውቅና-ካለው ካውንስሊንግ ኤጀንሲ (consulting agency) - ካገኘነው ድጋፍ እና እገዛ ጋር፤ የመረጃ-ስብስቡ/dataን የተነተነው፣ በጥልቅ ውይይት ውስጥ የተሳተፍን እና በተማሪ እና በሠራተኞች ስኬት ላይ - ትልቅ እና ከፍተኛ አዎንታዊ ተፅዕኖ ያላቸውን ቅድሚያ-የሚሰጣቸውን ጉዳዮች በመለየት፣ በአንድነት ሰርተናል። ውጤቱ፤ ነዋሪ-የሆነ፣ እያደገ-የሚሄድ እና በሁኔታዎች እየተሻሻለና-እየተለወጠ የሚሄድ ዕቅድ ሲሆን፣ በመጪዎቹ ዓመታት ውስጥ ያለንን ውሳኔዎች እና ኢንቬስትመንቶች - የሚመራ-ይሆናል።

### ቀጣይነት-ላለው መሻሻልን - ለማድረግ፣ የቃል-መግባት ቁርጠኝነት

የእኛ ስልታዊ ዕቅድ (strategic plan)፣ የአተገባበር-አፈፃጸሙ ያህል - ጠንካራ-ነው። ሂደታችን በምን-ላይ እንዳለ ለመከታተል፣ ተጽዕኖውን ለመለካት እና ማስተካከያዎችን ለማድረግ እና ማንኛውንም አስፈላጊ-የሆኑ ማስተካከያዎችን - በሂደት-ጉዞ ላይ እያለን ለማድረግ፣ በትጋት-እንሰራለን። የእኛ የአመራርነት ቡድን፣ ቁልፍ-የሆነ የክንውን-ሂደት ጠቋሚዎች/key performance indicators (KPIs) ላይ በመደበኛነት ምልከታ-የሚያደርግ እና፣ በማህበረሰቡ መካከል ግልጽነትን እና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ፣ አዲስና-ማሻሻያዎች (updates)ን ያጋራሉ።

ይህ ዕቅድ፣ የእኛ የACPS ማህበረሰብ — ተማሪዎቻችን፣ ቤተሰቦቻችን፣ ትምህርት-ሰጪዎቻችን እና የማህበረሰብ አጋሮቻችን፤ ለአጠቃላይ ስብስብ ጥረቶቹ፣ ምስክር-የሚሆን ነው።  ስለ ድምፃችሁ እና ለአበረከታችሁት አስተዋጽዖ እናመሰግናለን፤ ACPS ለበለጠ-ጠንካራ፣ የበለጠ ፍትሃዊ-እኩልነት ያለው እና ፈጠራዊ የትምህርት ቤት ክፍል/division እንዲኖር - ፍኖተ-ካርታውን ለማቅረብ ችሏል።

ለACPS ተማሪዎች እና ሠራተኞች ላሳያችሁት ምንጊዜ-ለማይቀየረው እርዳታ እና ቁርጠኝነታችሁ እና ለወደፊቱ ስላለን የጋራ ራዕይ፤ ያለኝን ልባዊ ምስጋና እና አድናቆት - ለመግለጽ እወዳለሁ።  በአንድላይ-ሆነን፤ እያንዳንዱ ልጅ - ለመማር፣ ለማደግ፣ ስኬትን-ለማግኘት እና ሙሉ-ለሙሉ ሊያገኙት-በሚችሉበት ደረጃ ለመድረስ የሚችሉበትን - የትምህርት ቤት ክፍል/divisionን በመደገፍ እና በመገንባት የምንቀጥል-ይሆናል። ይህንን ዕቅድ ለመፍጠር በተሰራው-ስራ እና ግቦቹን እውን-ለማድረግ - ከእኛ ጋር አጋርነትን-መፍጠራችሁን፣ እንደምታደንቁት - እርግጠኛ ነኝ።

ከሰላምታ ጋር፣



**ሚላኒ ኬይ-ዋየት (Melanie Kay-Wyatt)፣ Ed.D.**
የትምህርት ቤቶች ጠቅላይ-ሥራ አስኪያጅ

# ከ‘የአሌክሳንድርያ ከተማ ትምህርት ቤት’ ቦርድ፣

## የተላከ-መልዕክት

የእኛ ታዳጊ-የሆኑ ሰዎች መበልጸጋቸውን-ማረጋገጥ፤ እንደ ከተማነቱ - ለአሌክሳንድርያ ስኬት፣ በጣም አስፈላጊ-ነው። ለልጆቻችን ባለን ቁርጠኝነት ኩራት-ይሰማናል፤ ይህንንም - በሕዝብ ትምህርት ቤቶቻችን ውስጥ፣ ኢንቬስት በማድረግ - እናረጋግጣለን። የእኛን ገንዘብ/dollars ኢንቬስት ከማድረግ በተጨማሪም፣ የእኛን ጊዜ እና ጉልበትንም ኢንቬስት እናደርጋለን። እኛ፤ የሽሚዞቻችንን እጆታዎችን ወደላይ የምንሰበስብ፣ ወደ ስራ የምንሰማራ እና ከባድ-የሆኑ ፈተኝና-አስቸጋሪ ሁኔታዎችን የምንቋቋም - ማህበረሰብ ነን። ከፍተኛ-ጥራት ያለው የሕዝብ ትምህርት ቤት ስርዓትን መገንባት እና ጠብቆ-ማቆየት - የማህበረሰቡን እርዳታ-ይፈልጋል፤ እና ልጆቻችን - በእኛ በሁላችን ላይ ይተማመናሉ። እናንተ — አስተማሪ፣ የአውቶቡስ-አሽከርካሪ፣ አስተዳዳሪ፣ ተማሪ፣ ወላጅ፣ አገልግሎት-ሰጪ/custodian፣ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ/volunteer፣ ታክስ-ከፋይ/taxpayer፣ የትምህርት ቤት ቦርድ ወይም የከተማ ካውንስል አባል — ሆናችሁም-አልሆናችሁ፤ የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) አንዱ-አካል ናችሁ፣ እና እያንዳንዳችን - ጠቃሚ-የሆነ ሚናን እንጫወታለን። ይህን ስልታዊ ዕቅድ (Strategic Plan) ለማንበብ ጊዜ-መስጠታችሁ - ለልጆቻችን እና ለትምህርት ቤቶቻችን እንደምትጨነቁ ያሳያል። እናመሰግናለን።

ይህንን ዕቅድ ለማውጣት፣ ሆን-ብለን - በአቀራረባችን ላይ - በዓላማ ሰርተን-ነበር። የክፍሉ/divisionን ጠንካራ-ጎኖችን እና መሻሻያ-ያለባቸውን ነገሮች ለመገምገም፣ የመረጃ-ስብስብ (data) ላይ እና የማህበረሰብ አስተያየት ላይ - ጥልቅ-የሆነ ምልከታ በማድረግ ጀምረናል። በመቀጠልም፤ እንደ የትምህርት ቤት ክፍል/division በምን-ላይ እንደምንገኝ እና ወደየት-መሄድ እንደምንፈልግ - ሃሳባችንን ለማንጸባረቅ - ለበርካታ ወራት የተሰበሰቡትን፣ ስፋት-ያላቸውን የACPS ቡድንን እና የማህበረሰብ ተወካዮችን - ሰብስበናል።
የትምህርት ጉዟችን፣ በዚህ ሕያው-በሆነ ሰነድ ላይ ከካቷል፤ ይህም እንደ የትምህርት ቤታችን ክፍል/division የ‘North Star’ መመሪያ ፖሊሲ፣ በጀት፣ ፕሮግራም-አሰራር እና የተግባራዊ-ክንውን ውሳኔዎችን - በሚቀጥሉት ዓመታት ውስጥ አገልግሎት-የሚሰጠው ነው። እያንዳንዱ የዕቅዱ - ከፍተኛ-ስኬትን ለማግኘት-የወጡት ዓላማዎች፤ ወደ ተጨባጭ-የሆኑ እርምጃዎች እና መለካት-ወደሚችሉ ጠቋሚዎች - ተግባራዊ ይሆናሉ። ይህ መዋቅር፤ ለማህበረሰቡ፣ እኛ ለምን እየጣርን-እንደሆነ፣ የት-ላይ ማስተካከያ ማድረግ እንዳለብን እና እዚያ-ስንደርስ እንዴት ማወቅ-እንደምንችል - እንዲያውቁ - ግልፅነትን ይፈጥራል። ዕቅዱን በምናስፈጽምበት ጊዜ፣ ማህበረሰቡ - በምናደርገው የእድገት-ሂደት ላይ፣ መደበኛ-የሆነ አዲስና-ማሻሻዎች/updatesን፣ ያገኛሉ።

ለACPS ስልታዊ ዕቅድ-አወጣጥ ኮሚቴ (Strategic Planning Committee) እና ራዕያችንን፣ ዓላማችንን፣ እና ግቦቻችንን - አጣርቶ-ለመስራት አጋር-የሆኑን - ሰፊውን የአሌክሳንድርያ ማህበረሰብ፤ ከልብ-የመነጨ ምስጋናችንን እናቀርባለን። የእኛ አዲሱ ዕቅድ፤ የእኛን ዋናውን እሴቶች/core values ውስጥ መኖራችንን-መቀጠል የምንችልበት፤ እርምጃን-ያገናዘበ እና ቁልፍ-የሆኑ ልምምዶች (key practices)ን የሚገልጽ-ነው። እያንዳንዱን ግብ - እኛ-እራሳችንን ተጠያቂ-አድርገን ለመያዝ ከምንጠቀምበት - ከስልቶች እና ቁልፍ-የሆነ የክንውን-ሂደት ጠቋሚዎች/Key Performance Indicators (KPIs) ጋር ጎን-ለጎን አድርጎ የሚያስኬድ-ነው።

በዚህ-ዓመት መጀመሪያ-አካባቢ፤ ከተማችን በቅርቡ - የአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School) - ሚኔ ሃዋርድ ካምፓስ (Howard Campus) የዘመናዊነት-ስራ ላይ፣ አዲስ ታሪካዊ-ነጥብን አስቀምጣለች። በ1960 ውስጥ፣ ከዚህ-ቀደም ሙሉ-ለሙሉ ነጭ የነበረውን ሚኔ ሃዋርድ (Minnie Howard) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ፣ የተጣመሩትን አምስት ታዳጊ ጥቁር ተማሪዎችን - በማስታወስ-ያከበረ ነው። በአሌክሳንድርያ ውስጥ፣ ለሕዝብ ትምህርት በተገባው ቃል-ላይ፣ የሚፈለገውን ለማቅረብ ብዙ-ተጉዘን አልፈናል። የዛሬዎቹ ወጣቶች፤ የቀደሙ-አባቶቻችን ፈጽመው-ሊገምቱት በማይችሉት ዓለም ውስጥ - ሆነው፣ ወደ-አዋቂነት ዕድሜ እየተጓዙ-ነው። ከ‘አየር-ሁኔታ ለውጥ (climate change)’ እስከ ‘አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ (artificial intelligenc)’፣ ተማሪዎቻችን - አዳዲስ እና ውስብስብ ፈታኝና-አስቸጋሪ ሁኔታዎችን የመቋቋም ስራ-ያላቸው ሲሆን፣ እንዲሁም-ደግሞ - አስደሳች የሆኑ ዕድሎችን እያገኙ ነው። አሌክሳንድርያ፤ አስፈላጊ መመሪያን፣ ለእነዚህ-ዓይነት ሁኔታዎች አስፈላጊ-የሆኑትን - ችሎታዎችን እና እርዳታዎችን፤ ለእነርሱ-ለማቅረብ አስደሳች ኃላፊነት አለበት። በእኛ የእድገት-ሂደት (Our Progress) ላይ እንገባ፤ በዋናው እሴእቶቻችን-ላይ ዳግም-እንናረጋግጥ፣ እና የጋራ ራዕያችንን ለማሟላት-እራሳችንን ቃል-እናስገባ።

ከሰላምታ ጋር፣



**ዶ/ር ሚሼል ሪፍ (Dr. Michelle Rief)**
ሊቀ-መንበር

# ስለ አሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)

የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፤ ለሁሉም ተማሪዎች፣ ሁሉን-አቀፍ እና ደጋፊ-ሰጪ የሆነ የትምህርት አካባቢን ለማቅረብ በትጋት-የሚሰራ፣ ደማቅ-የሆነ እና ስብጥር-ያለው - የትምህርት ቤት ክፍል/division ነው። ከ16,300 በላይ - ተማሪዎችን አገልግሎት የሚሰጠው ACPS - ከ118 በላይ-አገሮች የመጡትን እና 127 የተለያዩ ቋንቋዎችን ከሚናገሩ ተማሪዎች ጋር-ሆኖ፣ ያለውን የበለጸገ የባህል ውስብስብነትና-ስብጥርን በሚያንጸባርቅ-መስራት በመቻሉ - ኩራት-ይሰማዋል።

**2024**

## የተማሪ የስነ–ሕዝብ ማንነት (Student Demographics)

*የምዝገባ ቁጥሮች - እስከ ሴፕቴምበር/September 2024 ድረስ (አጠቃላይ - የACPS ስርዓት/system - ከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት፣ መካከለኛ (middle) ትምህርት ቤት እና የመጀመሪያ-ደረጃ ላይ-የሚገኙት ክፍሎች - በአጠቃላይ ድምር)*

**16,335** አጠቃላይ ክፍል/Total Division

**4,634** ከፍተኛ–ደረጃ ትምህርት ቤት (ሁሉም፣ ከ9–12)

**3,432** መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት (ሁሉም ከ6–8)

**7,86** የመጀመሪያ–ደረጃ (ሁሉም ከPreK–5)

## 2024-25 አጠቃላይ የአባልነት–ምዝገባ (Membership)

| የክፍሉ አባልነት/Division Membership - በጎሣ/Ethnicity | የተማሪዎች ቁጥር |
|---|---|
| እስያዊ | 1,058 |
| ጥቁር | 3,817 |
| ሂስፓኒክ | 6,198 |
| ነጭ | 4,394 |
| ተወላጅ ሃዋይዋን (Native Hawaiian)/ፓስፊክ አይላንደር (Pacific Islander) | 55 |
| ተወላጅ አሜሪካውያን(Native American)/አላስካዊ (Alaskan) | 26 |
| ባለብዙ-የዘር ድብልቅ (Multi-Racial) | 787 |




**118** የትውልድ አገሮች

**127** የሚናገሩት የአፍ–መፍቻ ቋንቋዎች (Native Languages Spoken)

**47%** ነነፃ/ቅናሽ–ዋጋ ለተደረገላቸው – ምግቦች (Free/Reduced–Price Meals) ብቁ–የሆኑ ተማሪዎች

**38%** የእንግሊዘኛ ቋንቋን የሚማሩ

**12%** ከጉዳተኝነት ጋር የሚገኙ ተማሪዎች (Students with Disabilities)

በላቀ-ደረጃ ያለው የቀለም-ትምህርት ጥናቶች (Advanced Academic Studies) ውስጥ (ከዚህ-ቀደም ተሰጥዖ እና ስጦታ ያላቸው/Talented and Gifted ተብሎ-ይተወቅ የነበረ) ውስጥ የሚሳተፉ ተማሪዎች፣ በዓመቱ-ሙሉ ተለይተው-የሚወጡ እና በዓመቱ-መጨረሻ የስቴት/state ሪፖርት ላይ - ሪፖርት ይደረጋል። ለትምህርት ዓመት 2023-24፣ ጠቅላላው የተማሪ ቁጥር ውስጥ 12% የያዘውን - በዓመቱ-መጨረሻ ላይ ለስቴት/state ሪፖርት በተደረገው ሪፖርት ውስጥ፣ ከ16,425 በንቃት-ከሚሳተፉ ተማሪዎች ውስጥ - በላቀ-ደረጃ ያለው የቀለም-ትምህርት ጥናቶች (Advanced Academic Studies) ውስጥ፣ 1,965 ተማሪዎች ተለይተው-ወጥተዋል።

# ለስልታዊ ዕቅድ-አወጣጥ (Strategic Planning)፣ የእኛ የአሰራር-አቀራረብ

**በአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ውስጥ፣ የእኛ ስልታዊ ዕቅድ-አወጣጥ ሂደት፤ ለፍትሃዊ-እኩልነት/equity፣ ትኩረት/focus፣ ለመላመድ-አቅም/adaptability እና እርምጃ-ለመውሰድ/action - ባለው ቁርጠኝነት ውስጥ - መሠረት-ያደረገ ነው። እያንዳንዱ ውሳኔ እና ቅድሚያ-የሚሰጠው ነገር፣ እያንዳንዱ ተማሪ እግጅ-በጣም ጥሩ ትምህርት ማግኘት እንዳለበት - ባለን እምነት ላይ የተቀረጸ ነው፣ እና የወደፊት የጉዞ ሂደትን ለማስቀመጥ፣ በእኛ ፍትሃዊ-እኩልነት ለሁሉም 2025 (Equity for All 2025) ዕቅድ - ላይ፣ መሠረቱን ገንብተናል።**

የACPS ስልታዊ ዕቅድ (Strategic Plan)፣ ለትምህርት ቤት ክፍል/division እና ለትምህርት ቤት ቦርድ - እንደ መመሪያ ሰነድ ሆኖ የሚያገለግል-ሲሆን፣ ስለ በጀት አወጣጥ፣ የንብረት ድልድል እና ስለ አዳዲስ ተነሳሽነቶች ምርጫ - ውሳኔዎችን ይቀርፃል። ቅድሚያ-የሚሰጣቸውን ነገሮች ለማስቀመጥ፣ እድገትን ለመገምገም እና ሁሉም ጥረቶች ለተማሪ ስኬት ከጋራ ራዕያችን ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ፤ ግልጽ-የሆነ ማዕቀፍ (framework) ያቀርባል። የትምህርት ቤት-ደረጃን የማሻሻያ ዕቅዶች እና የክፍል-አቀፍ/division-wide ዕቅዶች፤ በስልታዊ ዕቅዱ/strategic plan ውስጥ - ከተዘረዘሩት ግቦች እና ስልቶች ጋር በቀጥታ-ይገናኛሉ፣ ይህም በስርዓቱ/system ዙሪያ፣ አንድነት እንዲፈጠር እና በጣም-አስፈላጊ በሆኑት ላይ እንድናተኩር ይረዳናል።

## 1 ፍትሃዊ-እኩልነት በዋናነት/Equity at the Core

ACPS ፍትሃዊ-እኩልነት (equity)ን - እንደ፣ "ተማሪዎች - በሚገኙበት ቦታ-ላይ ማግኘት እና ትምህርትን-ለማግኘት እንቅፋት-የሚሆኑ ነገሮችን ለማስወገድ፣ በንቃት መስራት-ነው" ሲል ይተረጉመዋል። ይህ መሪ-የሆነው መርህ፤ እያንዳንዱ ተማሪ—የቀደመ መነሻቸው ከየትም-ሆነ የት፣ ያላቸው አቅም ወይም ሁኔታቸው ምንም-ሆነ ምን—ለመበልጸግ-የሚያስፈልጋቸውን እርዳታ እና ዕድሎችን ማግኘታቸውን ያረጋግጣል።

## 2 በእኛ የእድገት-ሂደት (Our Progress) ላይ፣ መገንባት

ይህ ዕቅድ፣ ከመጀመሪያ-መነሻ የጀመረ አይደለም፤ በፍትሃዊ-እኩልነት ለሁሉም 2025 ዕቅድ (Equity for All 2025 plan) ተነሳሽነቶች እና ቁርጠኝነቶች ላይ - የሚገነባ-ነው። ACPS እስካሁን ያደረገውን-እርምጃዎች እና ያንን ሂደት ጥልቅ-ለማድረግ እና እንዲቀጥል-በማድረግ ላይ ያለውን ቁርጠኝነት - እውቅና-እንሰጣለን።

## 3 የበለጠ-ግድ ለሚለው ነገር፣ ቅድሚያ-መስጠት

ስልታዊ ዕቅድ-አወጣጥ (Strategic planning) - ትኩረትን ይፈልጋል። የመረጃ-ምንጮች (resources)ን እና ኃይልና-ጉልበት (energy)ን ወደእነዚህ ነገሮች-ዙሪያ መምራታችንን በማረጋገጥ፤ በተማሪ ስኬት ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ያላቸውን - በይበልጥ ወሳኝ-የሆኑ ነገሮችን ዙሪያዎችን ለይተናል።

## 4 ለስልት (Strategy) እና ባህል ለውጥ - ዕቅድ-ማውጣት

ዘላቂ-የሆነ ለውጥ፤ ሁለቱንም - በስርዓቶች/systems ላይ እና በባህል ላይ ትኩረት-ማድረግን ይጠይቃል። ይህ ዕቅድ - በክፍሉ/division ዙሪያ ያሉትን ለማሻሻያ-የሚሆኑ ቁልፍ-የሆኑ ስልቶችን የሚዘረዝር-ብቻ ሳይሆን፤ ነገር-ግን፣ የወደፊት ራዕያችንን የሚደግፉ - የጋራ አስተሳሰብን፣ እሴቶችን እና የስራ መንገዶችን - እንዴት እንደምናዳብርም ከግምት-ውስጥ ያስገባል።

## 5 በአፈፃጸ እና ቀጣይነት-ባለው ማሻሻያ ላይ፣ ትኩረት-አድርጎ መቆየት

ዕቅዱ ምንም-ጥሩ ሆኖ-ቢሰራም፣ የአፈፃጸሙ-ጠንካራነት ይወስነዋል። ACPS፤ ስልት/strategyን ወደ የድርጊት-እርምጃ ይለውጣል፣ እየተማርን ባለንበት-ጊዜ ላይ - የእድገት-ሂደቱን ይከታተላል እና የአሰራር-አቀራረባችንን በጥሩ-ሁኔታ እናጣራለን—ለተማሪ፣ ሠራተኞች እና ማህበረሰቡ ለሚፈልጓቸው-ነገሮች ምላሽ-ሰጪ ሆነን-መቆየታችንን ያረጋግጣል።

**ይህ ስልታዊ ዕቅድ (strategic plan) ከፍኖተ-ካርታ በላይ-የሆነ ነው—የእያንዳንዱ የACPS ተማሪን ለመንከባከብ፣ ለማስተማር እና ለማነሳሳት ያለንን ዓላማችንን ማሳካታችንን ለማረጋገጥ - እርምጃ-የመውሰጃ ጥሪ ነው።**

# የስልታዊ ዕቅድ-አወጣጥ ሂደት



**የACPS - ስልታዊ ዕቅድ (Strategic Plan)ን ማሳደግ፤ ትብብር-ማድረጊያ፣ ባለ-ብዙ የሂደት-ደረጃ የነበረ ሲሆን፣ ይህም ዕቅዱ የመላው የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ የሚያስፈልጓቸውን-ነገሮች እና ግቦች የሚያንፀባርቅ መሆኑን-ለማረጋገጥ፣ ሰፊ-የሆኑ ድምፆችን አሳታፊ-ያደረገ ነበር። በዚህ ሂደት ውስጥ-ባለንበት ጊዜ ውስጥ፣ ለእነዚህ ጥቂት ቁልፍ-የሆኑ እሴቶች - ቁርጠኞች-ሆነን እንቀጥላለን:**



## 1 በተማሪ፣ ቤተሰብ እና ሠራተኛ ድምፅ-ላይ፣ ያተኮረ

ዕቅዱ - በእውነታዎች፣ በተሞክሮዎች እና የምናገለግለው ማህበረሰብ በሚፈልጓቸው ነገሮች-ላይ መሠረት-አድርጎ የተመሰረተ መሆኑን-በማረጋገጥ - የእኛ ስራ በቀጥታ-ተፅዕኖ የሚያደርግባቸውን-ለማዳመጥ፣ ቅድሚያ-እንሰጣለን።




## 2 በመደበኛነት - መደጋገም እና ማስተካከል/Iterate and adjust regularly

ስልታዊ ዕቅድ አወጣጥ (strategic planning) የአንድ-ጊዜ ክስተት ሳይሆን፣ ተለዋዋጭነት/flexibilityን፣ ማንጸባረቅ/reflectionን የሚጠይቅ እና አዲስ-የሆኑ ፈታኝና-አስቸጋሪ ነገሮች እና ዕድሎች በሚመጡ-ጊዜ - ተላምዶ-ለመስራት ፈቃደኝነት-ማሳየትን የሚጠይቅ፣ ቀጣይነት-ያለው ሂደት መሆኑን እንገነዘባለን።



## 3 በመረጃ-ስብስብ ላይ፣ መህልቅን-መጣል/Anchor in data

ይህንን ዕቅድ - በመረጃ-ስብስብ (data) ጠንካራ-መሠረት ላይ፣ ማስረጃዎችን በመጠቀም ፈታኝና-አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ለመለየት፣ የእድገት-ሂደትን ለመለካት እና ትርጉም-ሰጪ የሆነ ማሻሻያዎችን ለማድረግ የሚመራውን - በደንብ አውቀውት የሚያደርጉትን ውሳኔዎች መወሰን (informed decisions) ላይ፤ ገንብተናል።



## 4 ለተሰጠው-አስተያየት (feedback)፣ አዕምሮን-ክፍት በማድረግ እና ለመማር

የተለያዩ የሃሳብ-አመለካከቶችን - በጥሞና በማዳመጥ እና ዕቅዱን ለማጠናከር የታሰበ ማስተካከያዎችን በማድረግ፣ በአስተያየት-የሚመራ ሂደት (feedback-driven process)ን፣ ተቀብለናል።

**እነዚህን እሴቶች/values በሚገባ-በማክበር፤ ACPS - እድገት-ማሳየቱን እና ተልዕኮውን በማሳካት እንዲቀጥል - ከትምህርት ቤቶቻችን፣ ተማሪዎቻችን እና ማህበረሰባችን ጋር፣ ጎን-ለጎን ሆኖ የሚያድገውን—ነዋሪ-የሆነውን ዕቅድ (living plan) ፈጥረናል።**

# የእኛ የጊዜ-አቀማመጥ እና ሂደት

**የሂደት-ደረጃ/PHASE 1**
ፀደይ (Spring)–በጋ/Summer 2024

**መሠረቱን መጣል/Laying the Foundation**

**የሂደት-ደረጃ/PHASE 2**
በልግ (Fall) 2024

**ዕይታዊ-አመለካከት ማድረግ እና የመንስዔው ትንታኔ**

**የሂደት-ደረጃ/PHASE 3**
ክረምት (Winter) 2024–2025

**ግቦችን እና ስልቶችን - በደንብ-ማጣራት**

**የሂደት-ደረጃ/PHASE 4**
ክረምት (Winter)ፀደይ (Spring) 2025

**የማህበረሰብ ተሣትፎ እና ማጠቃለያ-አድርጎ መጨረስ**

### የሂደት-ደረጃ/Phase 1: መሠረቱን መጣል/Laying the Foundation

ሂደቱ የጀመረው፣ ጥልቀት-ያለው የመረጃ-ስብስብ/data ምልከታ፣ ከሠራተኞች፣ ቤተሰቦች እና ተማሪዎች የተሰጡ አስተያየቶች እና የACPSን ጠንካራ-ጎኖች እና መሻሻል-ያለባቸው ነገሮች-ዙሪያን - ቁልፍ የክፍል/division ሰነዶችን በመገምገም ነው። ይህ መሠረታዊ-የሆነ ስራ፣ ለስልታዊ፣ የመረጃ-ስብስብ ማወቅ-የሚያስፈልጋቸው ነገሮች የማግኘት አቀራረብ(data-informed approach)ን ለዕቅድ-አወጣጥ መድረኩ-ትን-በማስቀመጥ፣ እርዳታ-አድርጓል። ዋና-የሆነ የዕቅድ-አወጣጥ - ቡድን (Core Planning Team)ን - የዕቅድ-አወጣጥ ሂደቱን ከመሩት ቁልፍ-በሆኑ የክፍል/division መሪዎች የተውጣጣውን፣ ከጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ (superintendent) እና የትምህርት ቤት ቦርድ ጋር ትብብር-በማድረግ፣ አቋቁመናል።

በዕቅድ-አወጣጥ ሂደቱ ውስጥ፣ ሰፊ-የሆነ ውክልና መኖሩን ለማረጋገጥ፣ ለስልታዊ ዕቅድ-አወጣጥ ኮሚቴ (Strategic Planning Committee (SPC)፣ የማመልከቻ ሂደትን - አስጀምረናል። ከየክፍሉ/division ዙሪያ፣ ከፍተኛ-የሆነ ፍላጎት ነበረን እና ስብጥር-ያለውን—ጂኦግራፊያዊ፣ ዘር፣ የትምህርት-ደረጃ (የመጀመሪያ-ደረጃ፣ መካከለኛ እና ከፍተ-ደረጃ) እና የይዘቱ ዙሪያ-ያሉ ባለሞያተኞችን - ቅድሚያ-የሚሰጥ፣ የምርጫ ሂደትን በመጠቀም ያለውን-ዝርዝር አጥብበነዋል። ከዚህ ሂደት ውስጥ፣ አባላቶች ተመርጠው ነበር፤ ይህም - ከሁሉም-ደረጃዎች/levels የተውጣጡ ሠራተኞች፣ ቤተሰቦች፣ ተማሪዎች እና የቦርድ አባላቶችን ያካተተ-ነው።

### የሂደት-ደረጃ (Phase) 2: ዕይታዊ-አመለካከት (Visioning) እና የመንስዔው ትንታኔ/Root Cause Analysis

ለ'ACPS' ተማሪዎች የወደፊት-ሁኔታ፣ የተጋራ ራዕይን ለመመስረት፤ 'SPC' ለመጀመሪያ-ጊዜ በኦክቶበር (October) 2024 ስብሰባ-ያደረገ እና የክፍሉ /division ን የመነሻ-ነጥብን ለመገንዘብ፣ አሁን-ያለውን የመረጃ-ስብስብ (data)ን ተንትኗል። በኖቬምበር (November) 2024 ውስጥ፣ ቁልፍ-ከሆኑት ፈታኝና-አስቸጋሪ ነገሮች ጀርባ-ያለውን የስር-መሠረቱን እውነታዎች ለመፈተሽ፣ ኮሚቴው የመንስዔ ትንታኔ (a root cause analysis)ን አካሂዷል። ይህ ትንታኔ፣ ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት - የእድገት ግቦችን እና ስልቶች (goals and strategies)ን በቀጥታ-ጠቁሟል።

### የሂደት-ደረጃ (Phase) 3: ግቦችን እና ስልቶችን - በደንብ-ማጣራት

በዲሴምበር (December) 2024 ውስጥ፣ የቀረቡትን ግቦች እና ስልቶች (goals and strategies) ለማጣራት እና ለማጠናከር፣ 'SPC' በድጋሚ ተሰብስቧል። ግቦቹ፤ ACPS **ምን** ለማሳካት ዓላማ-እንዳደረገ የሚገልጽ ሲሆን፤ በዚያን-ሁኔታ ደግሞ ስልቶቹ የክፍሉ/divisionን ዕቅዶችን - **እንዴት** እነሱን-ስኬታማ እንደሚያደርግ ይዘረዝራል። ስፋት-ያለው የማህበረሰብ አስተያየትን ለመሰብሰብ፣ ኮሚቴውም ዕቅድን-ያወጣል።

ይህ ሂደት በሚካሄድበት ጊዜ-ሙሉ፤ የACPS አመራር የውስጥ-ሠራተኞች/internal staffን በግብ ዓይነት-ምድቦች/goal teams አማካኝነት—የክፍል/division መሪዎች ቡድኖች - የመረጃ-ስብስብ/dataን፣ ነባር-የሆኑ ተነሳሽነቶችን እና ከ'SPC' የቀረቡ-ሃሳቦችን - ተመራጭ-ከሆኑ ልምምዶች እና የክፍሉ አቅም/division capacity ጋር ጎን-ጎን ሆኖ መሄዳቸውን-ለማረጋገጥ፣ ምልከታ-የሚያደርጉትን - ያሳትፋል። በተጨማሪም፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ ትምህርት ቤት ቦርድ (Alexandria City School Board) - የዓላማ እና የራዕይ ጽሁፎች/statementsን ለመቅረጽ እና በስልታዊ ዕቅዱ አካሄድ ላይ አስተያየትን ለመስጠት፣ በአውደ-ጥናቶች ውስጥ በመሳተፍ - ወሳኝ-የሆነ ሚናን ተጫውተዋል።

### የሂደት-ደረጃ (Phase) 4: የማህበረሰብ ተሣትፎ እና ማጠቃለያ-አድርጎ መጨረስ

በጃንዋሪ (January) እና ፌብሩዋሪ (February) 2025 መካከል-ባለው ጊዜ፤ ACPS - ጠንካራ-የሆነ የማህበረሰብ ተሣትፎ ጥረትን - በግምት 20 ፎከስ ግሩፕስ (focus groups)ን ያካተተ እና ከሠራተኞች፣ ቤተሰቦች እና ተማሪዎች - ከ240 ምላሽ-ሰጪዎች፣ የአስተያየት-መስጫ ቅጽን ሰብስቧል። ይህ አስተያየት፤ የዕቅዱን ግቦች እና ስልቶች ለግልጽ-ለማድረግ እና ለማጣራት ረድቷል። በፌብሩዋሪ (February) 2025 ውስጥ፤ 'SPC'፣ የባለድርሻ-አባልን አስተያየት (stakeholder feedback) አብሮ-እንዲካተት ለማድረግ፣ እና ተገቢ-የሆነውን ማስተካከያዎች ለማድረግ - የመጨረሻ-ስብሰባውን አካሂዷል።

ይህ-በእንዲህ እያለ፤ ACPS - ከሲኒየር አመራርነት ቡድን (Senior Leadership Team (SLT)፣ ከርዕሰ-መምህራን እና ከረዳት ርዕሰ መምህራን ጋር በመሆን፣ በባህል-ላይ ትኩረት ያደረገውን ስራውን ቀጥሏል። ይህ ስራ፤ ዋና እሴቶችን መግለፅ እና የዕለት-ተዕለት ልምዶችን እና ባህሪያትን በመለየት - ስልታዊ ዕቅዱን ወደ ህይወት በማምጣት-ላይ ማዕከል-ያደረገ ነው። በባህል እና ስልት/strategy መካከል ያለውን ጎን-ለጎን ሆኖ የመሄድ-ሁኔታን በማረጋገጥ፤ ACPS - ስኬታማ የሆነ አፈፃፀም እንዲኖር መሠረት እየጣለ ይገኛል።

# የእድገት-ሂደት ቁጥጥር-ማድረግ (Progress Monitoring)

አንድ-ጊዜ ዕቅዱን እንዳጠናቀቅን፣ የማስፈጸም-ስራው ይጀመራል። ሂደቱ፣ ከቁልፍ-የሆነ የክንውን-ሂደት ጠቋሚዎች/Key Performance Indicators (KPIs) ጋር ሲነፃጸር፤ ከጊዜ-በኋላ ቁጥጥር-የሚድረግበት እና ዓመት-ከዓመት በሆነ-ጊዜ ላይ ሪፖርት-ይደረጋል። ስለ ሂደቱ ለመወሰን በሚገባ-ለማሰብ፣ የሚያጋጥሙንን እንቅፋቶች ለመጋፈጥ፣ ችግሮችን ለመፍታት እና ወደፊት-ለመጓዥ የሚያስፈልጉ ማስተካከያዎችን ማድረግ የሚያስችለንን፤ ስለሂደቱ - መደበኛ የሆኑ ውይይቶችን - ለማድረግ በቁርጠኝነት ቃል-ግብተናል። እነዚህ “stocktakes” በመደበኛ አሰራር - በእያንዳንዱ ግብ ዙሪያ ባሉ መሪዎች እና በጠቅላይ-ስራ አስኪያጁ መካከል ይከናወናል። መደበኛ አዲስና-ማሻሻያዎች (regular updates)ን ለቦርድ እና ለመላው ሕዝቡ - በሁለቱም - በመረጃ-ስብስብ ውጤቶች (data outcomes) እና አፈፃፀሙ እንዴት እየሄደ እንደሆነ- በተመለከተ፣  ያለውን የእድገት-ሂደትንም የምናቀርብ ይሆናል።



# የእኛ ስልታዊ ዕቅድ (Our Strategic Plan)

ዕቅዳችን፤ የክፍላችን/divisionን አቅጣጫ በመቅረጽ፣ የስልታዊ እና ባህላዊ - የሁለቱንም - አስፈላጊነት እውቅና-ይሰጣል። አጠቃላይ-በሆነው ዓላማችን ኃይል-የምናገኝ ሲሆን፣ የእኛ “ለምን/why” የሚለው-ጥያቄያችን - በተልዕኮአችን/mission እና በራዕያችን/vision የጽሁፍ-መግለጫችን ተተርጉሞ-የተፃፈ ነው። የእኛ ግቦች - ወደዚያ ተልዕኮ እና ራዕይ እድገት ለማድረግ፣ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ውስጥ ምን ማከናወን እንዳለብን ይገልፃሉ። እያንዳንዱ ግብ የሚለካው፤ በእያንዳንዱ የግብ ዓይነት-ዙሪያ ውስጥ እድገታችንን ለመከታተል የምንጠቀምባቸው ከፍተኛ-ደረጃ ባላቸው - ቁልፍ-የሆኑ የአፈጻጸም ጠቋሚዎች (key performance indicators (KPIs) ስብስብ-ላይ ትኩረት-በማድረግ ነው። ከዚያም-በመቀጠል፤ የእኛ ስልቶች የሚገለጹት፤ በእነዚህ ግቦች - እንዴት ውጤታማ እንደምንሆን፣ ትኩረት-ያለውን የምንሰራበትን መንገድ ላይ ለውጥ-በማስቀመጥ ነው። እነዚህ ስልቶች፤ በውስጣዊ አሰራር - በግብ ዓይነት-ምድቦች/goal teams ውስጥ፣ ቡድኑ በሚቀጥሉት አምስት-ዓመታት ውስጥ ተግባራዊ በሚያደርጋቸው ልዩ ፕሮጀክቶች ወይም ተነሳሽነት - ተከፋፍልረዋል።

ይህ በእንዲህ-እያለ፣ የዚህ ዕቅድ አንዱ-አካል ሆኖ፣ ባህላችንን ለመቀየር - ሆን-ብለን እየሰራን ነው። የእኛ - ዋና እሴቶቻችን - እንዴት ባህሪያችንን እንደምናሳይ እና ለምን ቁርጠኝነት-እንዳለን ያሳያል። ባህሉ - እንደ ሠራተኞች - ከእኛ-ጋር ይጀምራል፤ ስለሆነም፣ በመጀመሪያ - ከእነዚህ እሴቶች ጋር ጎን-ለጎን ሆኖ በሚሄድ ሁኔታ የእኛ-የራሳችንን ባህሪይ እንዴት-ለመቀየት እንደምንችል ትኩረት-አድርገናል። እያንዳንዱ ዋና እሴት/core value፤ ወደ ሕይወት የመጣው፣ ቁልፍ-የሆኑ ልምምዶች (key practices) ስብስብ-አማካኝነት ሲሆን፣ እነዚህን እሴቶች በየቀኑ እንዴት እንደምናሳይ የሚገልጽ-ነው። በውስጣዊ-አሰራር፣ እነዚህን ዋና ልምምዶች/core practices በይበልጥ-ተለይተው ሊታዩ-ወደሚችሉ ባህሪያት ከፋፍለናቸዋል፣ ይህም ለቅጥር-ባለን ስርዓታችን ውስጥ፣ በግምገማ እና የተቀጣሪ-ሠራተኛ እውቅና-መስጫ ውስጥ ከተካተተ-ይሆናል።



# የእኛ ባህል/Our Culture




የእኛ - ዋና እሴቶቻችን፣ የACPSን መሠረታዊ-የሆነውን እምነቶች፣ የሚዘረዝር ነው። እነዚህን እሴቶችን፣ በእኛ ባህል ውስጥ ለማካተት-እንዲቻል፤ እነዚህን እሴቶች፣ ሁሉም ተቀጣሪ ሠራተኞች፣ ዕለታዊ-በሆነው አሰራር ውስጥ እንዴት ማሳየት-እንዳለባቸው መመሪያ የሚሰጠውን - ተዘጋጅቶ-የተቀመጠውን ቁልፍ-የሆኑ ልምዶችን ለይተን-አስቀምጠናል። በውስጣዊ-አሰራር ውስጥም፣ ለሠራተኞች - መለካት-የሚችለውን እና ምልከታ-ሊደረግባቸው የሚችሉትን - አብረው-ጎን ለጎን ሆነው የሚሄዱትን ባህሪያቶችንም ቀርጸናል።

**ዋና እሴቶች/Core Values: በምንሰራው-ነገር ሁሉ፣ የACPS መማሪያ ማህበረሰብ - እነዚህን ዋና እሴቶችን - ይዞ-ለመኖር እየገፋበት ነው። እኛ...**

## ሁሉን-ተቀባይ የሆነ (Welcoming)

በACPS ውስጥ፣ ሁሉንም ባለድርሻ-አባላቶች (stakeholders) - ደህንነታቸው-የተጠበቀ እና በደስታ-እንደተቀበልናቸው (welcomed) ስሜት እንዲሰማቸው፣ ንቁ እርምጃዎችን እንወስዳለን። በእኛ በር-በኩል የሚመጡትን ሁሉ-ተቀብለን፤ ልዩነቶቻችንን እናከብራለን - ምክንያቱም ልዩነታችን ትልቁ ጥንካሬያችን ነው-ብለን ስለምናምን ነው።

**ቁልፍ-የሆኑ ልምዶች (KEY PRACTICES)**

- **ግንኙነትን-መገንባት (Build Connection):** ደማቅ-አቀባበል ያለው፣ ሁሉን አካታች-የሆነ አካባቢን ለመፍጠር፤ ሆን-ተብሎ - ከተማሪዎች፣ ቤተሰቦች እና የስራ-ባልደረቦች ጋር መሳተፍ።
- **ያለውን ልዩ-የሆነ ማንነት - ማክበር (Celebrate Identity):** ስብጥር-ያለውን የቀደመ-መነሻዎች/diverse backgrounds እውቅና-መስጠት እና ማክበር፣ በማህበረሰቡ-ውስጥ ያለውን ሰው-በሙሉ ማጠናከር እና ልምድን-እንዲያገኝ-ማድረግ።

## ፍትሃዊ-እኩልነት ላይ ትኩረት ያደረገ (Equity-focused):

ትምህርትን-ለማግኘት እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን - በንቃት ለማስወገድ እንሰራለን።

**ቁልፍ-የሆኑ ልምዶች (KEY PRACTICES)**

- **ከራስ መጀመር:** በእያንዳንዱ-ግለሰብ ማንነት እና አድልዎ ላይ ማንጸባረቅ እና ይህ በውሳኔ-አሰጣጥ ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያደርግ-መመልከት።
- **እንቅፋቶችን ማስወገድ:** ዕድል-ለማግኘት - ስልታዊ-የሆነ እንቅፋቶችን ለመለየት እና ምላሽ-ለመስጠት፣ የመረጃ-ስብስብ (data)ን መጠቀም።
- **የዕይታ-አመለካከትን መጠየቅ:** ዕድልን-ከማግኘት በእጅጉ-ለራቁት፣ ድምፆቻቸውን ከፍ-እንዲል ማድረግ።



## ኃይልና-ጉልበት የሚሰጥ (Empowering)

እያንዳንዱን ተማሪ እና የሠራተኛ-አባል፤ ተመራጭ ወደሆነው አቅማቸው እንዲደርሱ፣ ስሜታቸውን-እናነሳሳለን።

**ቁልፍ-የሆኑ ልምዶች (KEY PRACTICES)**

- **በእድገት-ላይ ኢንቬስት-ማድረግ (Invest in Growth):** የስራ-ባልደረቦች እና ተማሪዎች - በጊዜ-ሂደት ውስጥ እንዲያድጉ ድጋፍ-የሚሰጣቸውን፣ ወቅታዊ-የሆነ አስተያየት/feedback እና የመማሪያ ዕድሎች/learning opportunitiesን - እርምጃ-መውሰጃዎችን ማቅረብ።
- **የራስን-ውሳኔ የማድረግ ነፃነት ከተጠያቂነት ጋር (Autonomy with Accountability):** ሠራተኞችን፤ ለውጤቶቹ እነርሱ-ኃላፊነትን እንዲወስዱ እያደረጉ-በመያዝ፣ ስኬትን ከሚያገኙበት መሣሪያዎች/tools ጋር - እገዛ-መስጠት።



## ፈጠራዊ-የሆነ (Innovative)

በመማሪያ-ክፍል ውስጥ እና በስርዓቱ ዙሪያ ባሉት-ነገሮች ውስጥ፣ ችግሮችን-ለማስወገድ - ተነሳሽነትን እንፈጥራለን።

**ቁልፍ-የሆኑ ልምዶች (KEY PRACTICES)**

- **በአንድነት፣ የበለጠ-ጥንካሬ ማግኘት/Stronger Together:** በተለያዩ ዓይነት-ዙሪያ ባሉ ነገሮች/across teams - የሃሳብ አመለካከትን እና በሚያመጣው ተጽዕኖ-ላይ የበለጠ-ደረጃ ላይ አድርሶ - ጎን-ለጎን ማስኬድን ለማጠናከር፣ ከእርስ-በርስ ጋር መስራት።
- **ዋና-መሪ ተማሪ መሆን/Be a Lead Learner:** የማወቅ ጉጉት፣ የማሻሻያ ሃሳቦችን ፈትኖ-መሞከር እና ቀጣይነት-ካለው በማንጸባረቅ-ከመመልከት - ከስህተቶች መማር።



## በውጤት-ላይ ያተኮረ (Results-Driven)

ለመማር፣ ለማደግ እና በከፍተኛ-ደረጃዎች ውጤታማ ለመሆን - ትልቅ-ተስፋ ያላቸውን ግቦ አስቀምጠናል።

**ቁልፍ-የሆኑ ልምዶች (KEY PRACTICES)**

- **በግብን ያገናዘበ/Goal Oriented:** ሁሉም-ሰው ስለ ዕድገት እውነተኛ-የሆነ አመለካከት እንዲኖረው በማረጋገጥ-ላይ፣ ግቦችን በግልጽ ማስቀመጥ እና የመግባባት-ግንኙነት ማድረግ።
- **በመረጃ-ስብስብ ላይ-መሠረት ያድረገ ውሳኔ/Data Informed:** በሁሉም ውሳኔዎች ውስጥ፣ ያለማቋረት - የመረጃ-ስብስብ (data) ላይ ምልከታ ማድረግ እና መጠቀም።



# የእኛ ግቦች/Our Goals

ተልዕኳችንን እና ራዕያችንን ለማሳካት፣
በሚከተሉት-ነገሮች ዙሪያ - ትኩረት አድርገናል።

# ተማሪዎች፤ ግንኙነት-ያደረጉ (connected)፣ እገዛ-ያገኙ፣ እና የተከበሩ-ዓይነት ስሜትን የሚያገኙበት፤ ደህንነቱ-የተጠበቀ፣ እንክብካቤ-ያለው እና ሁሉን-አካታች-የሆነ - የትምህርት ቤት አካባቢን መፍጠር።



**ምን:** እያንዳንዱ ተማሪ፣ በትምህርት ቤታቸው አካባቢው ውስጥ፣ ደህንነቱ-የተጠበቀ ስሜት - በሁለቱም - በአካላዊ እና በስሜታዊነት - እንዲሰማው ለማረጋገጥ፣ በቁርጠኝነት ቃል-ገብተናል።
 ይህም ማለት፤ ተቀባይነትና-አክብሮትን የሚያገኙበት ባህልን እና ስሜታዊ ጤናማነት ማዳበር፣ ግልጽ-የሆነ በባህሪያዊ-ሁኔታ የሚጠበቁ-ነገሮችን ማቅረብ እና ሠራተኞች - ከተማሪዎች ጋር ጠንካራ-ግንኙነቶችን የሚፈጥሩበት መሣሪያዎች/toolsን እና ጊዜን እንዲያገኙ-ማድረግ።

**ለምን:** ተማሪዎች ግንኙነት-ያላቸው (connected) እና ጥበቃ-የተደረገላቸው ሆኖ ሲሰማቸው፤ በተሻለ ለመማር እና ለመበልጸግ ይችላሉ። ሆኖም-ግን፤ የመረጃ-ስብስብ (data) እንደሚያሳየው፤ ሁሉም ተማሪዎች በአካላዊነት ወይም በስሜታዊነት በትምህርት-ቤት ውስጥ የደህንነት-ጥበቃ ያላቸው ሆኖ አይሰማቸውም። ጠንካራ-የሆኑ ግንኙነቶች፣ ሁሉን-አካታች ልምምዶች እና ግልጽ የባህሪይ ድጋፎችን ቅድሚያ-በመስጠት፤ ለቀለም-ትምህርት ስኬት እና ለጤናማነት መሠረትን-እንፈጥራለን።

**ቁልፍ-የሆነ የከንውን-ሂደት ጠቋሚዎች/KEY**

- ⬇**መቀነስ/Reduce፤** ስር-የሰደደ መቅረት/chronic absenteeismን መቀነስ (የቨርጅኒያ የትምህርት መምሪያ/Virginia Department of Education - የመረጃ-ስብስብ/Data)
- ⬆ **መጨመር/Increase፤** የሁለተኛ-ደረጃ ተማሪዎችን - “I feel safe during school” ከሚለው ጋር ያላቸውን ስምምነት የሚገልጸውን ከመቶኛ-ደረጃ/percentage መጨመር (የተማሪ የዳሰሳ-ጥናት)
- ⬇ **መቀነስ/Reduce** የተማሪ የደህንነት-ጥበቃ ክስተቶችን - መቀነስ (ለምሳሌ፤ ድብድብ/ጥቃቶችን-ማድረስ፣ የጦር-መሣሪያዎች/weapons፣ ማስፈራራቶች/ threats) (የትምህርት ቤት የደህንነት-ጥበቃ የመረጃ-ስብስብ/Data ምልከታ)

**ቀደምት-የሆኑ ስልቶች/PRIORITY**

**የተቀናጁ የድጋፍ-አሰጣጥ ስርዓቶችን ማጠናከር፤** ለተማሪዎች - በማህበራዊ እና ስሜታዊ ጤናማነት ላይ - አዎንታዊ-የሆነ ግንኙነቶችን ከእኩዮች እና ከሚታመኑ አዋቂዎች ጋር በመገንባት ላይ እያሉ፤ ማጠናከር።

**ግልጽ-የሆነ በባህሪይ የሚጠበቁባቸውን-ነገሮች፣ መፍጠር እና ተጠያቂ-ማድረግ፤** የእያንዳንዱን ተማሪ ልዩ-የሆነ የቀለም-ትምህርት እና በማህበራዊ-ስሜታዊነት የሚያስፈልጉ-ነገሮች ላይ በመርዳት ላይ-እያሉ፤ ይህን-ማስቀመጥ።

# የቀለም-ትምህርት የላቀ-ደረጃን ለማግኘት፣ እያንዳንዱን ተማሪ ማሳተፍ እና የመስራት-አቅማቸውን መፈተን።



**ምን:** እያንዳንዱ ተማሪ፤ ምክንያቲያዊ-በሆነ አስተሳሰብ እንዲያስብ እና ሙሉ በቀለም-ትምህርት መድረስ-የሚገባቸው አቅማቸው-ላይ እንዲደርሱ የሚያዘጋጃቸውን፤ ጠንከር-ያለ፣ አሳታፊ እና የተለየ የትምህርት-አሰጣጥ ተሞክሮዎችን ማግኘታቸውን - እናረጋግጣለን። ይህ፤ ምክንያቲያዊ-በሆነ አስተሳሰባቸውን እና ስሜቶቻቸውን የመቆጣጠር ችሎታቸውን ማዳበርን፣ በራስ-መተማመንን መገንባት እና ከACPS የተማሪ መገለጫ (Profile of a Learner) ጋር ጎን-ለጎን ሆኖ በሚሄድ-ሁኔታ - ከሌሎች ጋር መግባባትን ያካትታል።

**ለምን:** ከሁሉም ተማሪዎች ከፍተኛ-የሆነ የሚጠበቁባቸውን ነገሮች በማስቀመጥ እና እነዚያን እንዲያሟሉ መደገፍ፣ ለስኬታማነታቸው አስፈላጊ እንደሆነ እናምናለን። ሁሉንም ተማሪዎቻችንን - በተለይ-ደግሞ - በተለምዶ የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች በበቂ-ሁኔታ ያላገኙ ሕዝቦች (underserved populations)ን፤ እንደ - ቀለም-ያላቸው ተማሪዎች (students of color)፣ በኢኮኖሚያዊ-ሁኔታ ዕድል-ያላገኙ/economically-disadvantaged ተማሪዎች፣ የእንግሊዘኛ-ቋንቋን የሚማሩን እና ጉዳተኝነት-ጋር የሚገኙ ተማሪዎች - በጥሩ-ሁኔታ እያገለገልን እንዳልሆነ፣ የእኛ የመረጃ-ስብስብ (data) ያሳያል። የምርምር-ጥናቶች እንደሚያሳዩት፤ አሳታፊ፣ ጠንከር-ያለ የትምህርት-አሰጣጥ፣ እነዚህን-ያሉትን ክፍተቶች ለመዝጋት እና ሁሉንም ተማሪዎች ስኬታማ ለማድረግ፣ በጣም-አስፈላጊ ነው።

**ቁልፍ-የሆነ የክንውን-ሂደት ጠቋሚዎች/KEY**

- ⬆ ፕሮጀክት-የተደረገውን እድገት በማምጣት - (Measures of Academic Progress (MAP) ንባብ/Reading) ያሟሉ ወይም ከተቀመጠው-በላይ ያመጡ፣ ተማሪዎችን ከመቶኛ/percentage **ማሳደግ/Increase**
- ⬆ ፕሮጀክት-የተደረገውን እድገት በማምጣት - (MAP ሂሳብ/Math) ያሟሉ ወይም ከተቀመጠው-በላይ ያመጡ፣ ተማሪዎችን ከመቶኛ/percentage **ማሳደግ/Increase**
- ⬆ ለንባብ 'Standards of Learning (SOL)' (VDOE Data)፣ አጠቃላይ የማለፊያ-መጠን/pass rateን **ማሳደግ/Increase**
- ⬆ የሂሳብ/Math 'SOL' (VDOE Data)፣ አጠቃላይ የማለፊያ-መጠን/pass rateን **ማሳደግ/Increase**
- ⬆ በክፍል-ደረጃቸው የሚጠበቅባቸውን እያገኙ ላልሆኑ ተማሪዎች (MAP ንባብ/Reading) ዕድገትን **ማፋጠን/Accelerate**
- ⬆ በክፍል-ደረጃቸው የሚጠበቅባቸውን እያገኙ ላልሆኑ ተማሪዎች (MAP ሂሳብ/Math) ዕድገትን **ማፋጠን/Accelerate**
- ⬆ በእንግሊዘኛ-ቋንቋ የላቀ-ደረጃ ብቃት/English proficiency ላይ - የዕድገት ዒላማዎቹን ለማሟላት (World-Class Instructional Design & Assessment)፣ የእንግሊዘኛ-ቋንቋን የሚማሩ (English Learners) ተማሪዎች ከመቶኛ/percentage - **ማሳደግ/Increase**
- ⬆ ከACPS የተማሪ መገለጫ/Profile of a Learner ጋር ጎን-ለጎን ሆኖ በሚሄድ ሁኔታ (Measurement in Process) በተማሪን ድምጽ እና ኤጀንሲ/agency ላይ - **ማሳደግ/Increase**

**ቀደምት-የሆኑ ስልቶች/PRIORITY**

የተማሪዎችን ስብጥር-ያለውን ባህሎች በማንጸባረቅ፣ የማህበራዊ እና ስሜታዊ እድገታቸውን በመደገፍ እና እያንዳንዱ-ተማሪ ስኬት-ለማግኘት የሚያስፈልገውን ማግኘቱን-በማረጋገጥ፤ **ከፍተኛ-ጥራት ያለውን የመማሪያ ቁሳቁሶች/materialsን እና የማስተማር ልምዶችን መጠቀም**።

እንደ ጠንካራ-የሆኑ የትምህርት-አሰጣጥ አሰልጣኞች/instructional coaches እና ለትምህርት-ሰጪዎች መካሪዎች/mentors for educators ሆኖ ለማገልገል፤ (ርዕሰ-መምህራን፣ ረዳት ርዕሰ-መምህራን እና የትምህርት-አሰጣጥ አሰልጣኞች/instructional coaches) - **በትምህርት ቤት መሠረት-ያደረጉ የትምህርት-አሰጣጥ የአመራር ቡድንን - ኃይልና-ጉልበት መስጠት**።

# ስብጥር-ያለውን፤ ተሰጥዖ-ያለውን የባለሞያተኞች ቡድንን - እገዛ-ሰጪ በሆነ እና እድገትን-በአመላከተ የስራ-ቦታን በማቅረብ፣ በቅጥር-መቅጠር፣ ማሳደግ እና በቅጥር-ላይ ማቆየት።




**ምን:** የእኛን ስብጥር-ያላቸውን የተማሪ ቁጥርን የሚያንጸባርቁ እና በተሰጣቸው ሚናዎች ላይ ትልቅ-ዋጋ እንዳላቸው የሚሰማቸውን - ከፍተኛ-ጥራት ያላቸውን ትምህርት-ሰጪዎች እና ሠራተኞች፤ እንዲገቡ እንማርካለን፣ እናሳድጋለን እና በቅጥር-ጠብቀን እናቆያለን። ይህም፤ እያንዳንዱ ሠራተኛ እንዲበለጽግ - ቀጣይነት-ያለው ሙያዊ ትምህርት፣ የአመራርነት ዕድሎችን፣ ተወዳዳሪነት-ያለውን ማካካሻ እና ትርጉም-ያለው የድጋፍ ስርዓቶችን መስጠትን - ይጨምራል።

**ለምን:** የእኛ ሠራተኞች፣ የትምህርት ቤቶቻችን ዋናው-ክፍል ናቸው፤ ስለሆነም - እነርሱ ያላቸው ስኬት፣ በቀጥታ የተማሪን ውጤቶች ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል። ሆኖም፤ በተለይ-ደግሞ ወሳኝ-በሆኑት የስራ-ሚናዎች-ላይ፣ ሠራተኞችን በቅጥር-ማቆየት አስቸጋሪና-ፈታኝ ሆኖ ቆይቷል። ትምህርት-ሰጪዎችን - ድጋፍ-የሚያገኙ ሆኖ እንዲሰማቸው እና ጉልበትና-ኃይል የሚሰጣቸውን አካባቢ በመፍጠር፤ ከፍተኛ-ጥራት ያለው ትምህርት፣ ለሁሉም ተማሪዎች የመስጠት አቅማችንን እናጠናክራለን።

## ቁልፍ-የሆነ የክንውን-ሂደት ጠቋሚዎች/KEY

- ⬆ በትክክል የኮንትራት ውል የሚፈርሙ - ተመራጭ-የሆኑ እጩዎችን ከመቶኛ/percentage (Hiring Data) **ማሳደግ/Increase**
- ⬆ ፈቃድ-ያላቸውን ሠራተኞች (licensed staff) በቅጥር-የማቆየት የመጠን-ደረጃን - (Retention Data) **ማሳደግ/Increase**
- ⬆ በሠራተኞች ሪፖርት-ማድረግን - "ACPS [ለእነርሱ/their] ለሙያ-ማሳደጊያ፣ ዕድሎችን ይሰጣል" (የሠራተኛ የዳሰሳ-ጥናት) **ማሳደግ/Increase**

## ቀደምት-የሆኑ ስልቶች/PRIORITY

**ተሰጥዖ-ያላቸውን ባለሞያተኞች በቅጥር-ጠብቆ ማቆየት፤** ከእነርሱ ጋር እና ከዩኒየኖቻቸው/unions ጋር አጋርነትን-በመፍጠር፣ ጤናማነታቸውን በመደገፍ፣ የአመራርነት ዕድሎችን በመስጠት እና ተወዳዳሪነት ያለውን ክፍያ-በመክፈል።

**የበለጠ ትኩረት ያለው፣ ከሌላ-የተለየ የመማር ዕድሎችን ማቅረብ፤** ለትምህርት-ሰጪዎች - በሁሉ-ነገር በደንብ ከተዘጋጀው ሠራተኛ ጋር - ዕድሉን-በሚገባ ያላገኙ ተማሪዎች (underserved students) የሚያስፈልጓቸውን ለማሟላት - ከተሰጠ-ትኩረት ጋር - ማቅረብ።

**የቅጥር እና የማስተዋወቂያ ሂደቶች/orientation processesን ማሻሻል እና ቀልጣፋ-ማድረግ፤** የበለጠ ውጤታማ እና የተቀናጁ እንዲሆኑ ለማድረግ።

# ራዕያችንን ለማሳካት - ከማህበረሰባችን ጋር - በመሳተፍ እና በግልፅ በመነጋገር፣ እምነትን ማጎልበት።




**ምን:** ግልፅ፣ ወጥነት-ያለው የሁለትዮሽ-መንገድ ግንኙነት-ማድረግን፣ ትርጉም-ሰጪ የሆነ ተሳትፎ እና ወቅቱን-የጠበቀ እና ምላሽ-ሰጪ አገልግሎት ላይ በማተኮር፤ ከተማሪዎች፣ ቤተሰቦች እና ከሰፊው የአሌክሳንድርያ ማህበረሰብ ጋር - መተማመንን እና አጋርነትን - እናጠናክራለን።

**ለምን:** የእኛ ስብጥር-ያለው ማህበረሰብ፣ የእኛ-ጠንካራ ጎናችን እንደሆነ እናምናለን። እምነትን ለመፍጠር እና ከማህበረሰባችን ጋር ግንኙነት-ለመፍጠር መደበኛ ዕድሎችን ለማቅረብ-የምንችልበትን - እድገት-ማሳየት የምንችልበት ሁኔታ-እንዳለን - የእኛ የመረጃ-ስብስብ (data) ያሳያል።

ለግልጽነት - ቅድሚያ-በመስጠት፣ ቤተሰቦችን - በልጆቻቸው ትምህርት ውስጥ እንደ አጋሮች-ሆነው እንዲገኙ ኃይልና-ጉልበት በመስጠት እና በርካታ የግንኙነት-ማድረጊያ መንገዶችን በመስጠት - ሁሉም ተማሪዎች ስኬታማ ለመሆን የሚያስፈልጋቸውን የጋራ-ድጋፍ ማግኘታቸውን እናረጋግጣለን።

## ቁልፍ-የሆነ የከንውን-ሂደት ጠቋሚዎች/KEY

